# MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
# 2024–2025 CAFETERIA NEWS & MEALS INFORMATION
# የካፍቴሪያ ዘገባ እና የምግብ ዝርዝር መረጃ
# የማህበረሰብ ብቁነት በማሟላት ለሚሳተፉ ት/ቤቶች

**ልጆች ለመማር ጤናማ ምግብ ያስፈልጋቸዋል።** የምግብ እና የአልሚ ምግብ አገልግሎት ክፍል በየዓመቱ ከ18 ሚሊዮን በላይ ምግቦችን ያቀርባል። ለተማሪዎች ጤናማ የምግብ አማራጮችን እናዘጋጃለን፥ እንዲሁም አልሚ ምግቦች በተማሪዎች ዘንድ ተወዳጅነት እንዲኖራቸው ለማሻሻል በተከታታይ አዳዲስ መንገዶችን እንቀይሳለን።60 ትምህርት ቤቶች የማህበረሰብ ብቁነት መስፈርት (CEP) ያሟሉ በመሆናቸው በየቀኑ ቁርስ እና ምሣ ያለምንም ክፍያ ማግኘት እንደሚችሉ DFNS በደስታ ይገልጻል። ተማሪዎች በየቀኑ ተበረታተው መማር እንዲችሉ በትምህርት ቤት ቁርስ እና ምሳ እንዲመገቡ እናበረታታለን።CEP የትምህርት ቤቶች ዝርዝር እና ስለ CEP ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃዎች MCPS ድረ ገጽ ላይ ይገኛል።

## ከቁርስ እና ምሳ በተጨማሪ በግዢ የሚቀርቡ ምግቦች እና መጠጦች ይኖራሉ።

## "A LA CARTE FOODS AND BEVERAGES"

በተማሪዎ ትምህርት ቤት ካፍቴሪያ ከምግብ ዝርዝር ላይ የሚመረጡት ልዩ ልዩ አይነት (a la carte) ምግቦችም ይኖራሉ። ለሽያጭ የሚቀርቡ ምግቦች በሙሉ JPG-RA *ይከተላሉ። መልካም ጤንነት፦ አካላዊ እና ጤናማ አመጋገብ* በእያንዳንዱ ት/ቤት የተወሰኑ ነገሮች ይለያያሉ። በልጅዎ ት/ቤት ስለሚገኙ ምግቦች፣ ከምግብ ዝርዝር ላይ የሚታዘዙ እና የሚከፈልባቸው ምግቦች /la carte items፣ የግዢ መጠን ለመገደብ፣ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እባክዎ የት/ቤትዎን ካፍቴሪያ ማናጀር ያነጋግሩ።

ክፍያ የሚፈፀመው በጥሬ ገንዘብ፣ ወይም ለተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት ካፊቴሪያ አካውንት ምግብ በሚገዙበት ጊዜ ወይም በማንኛውም ጊዜ ኦንላይን የቅድመ ክፍያ ስርዓት በመከተል ነው። ካፍቴሪያዉ የክፍያ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሚያገለግል ስለሆነ በኮምፒውተር የታገዘ የካሽ ሪጅስተር ክፍያ ስርዓት መጠቀሙን ይቀጥላል። ገንዘብን በካፊቴሪያ አካውንት ውስጥ አስቀድሞ ማስገባት ተማሪዎች "a la carte" ከምግብ ዝርዝር ውስጥ ለሚፈልጉት ግዢ በየጊዜው ገንዘብ ይዞ መጓዝን ያስቀራል። **ተማሪዎች ከአካውንታቸው ክፍያ ለመፈፀም MCPS የተማሪ መለያ ቁጥራቸውን ይጠቀማሉ** (ትምህርት ቤቶች በተማሪ መታወቂያ ካርዶች ላይ የሚገኙ ባርኮዶችን ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የምግብ ካርዶችን) ካሽ ሪጅስተር ላይ ስካን ለማድረግ መጠቀም ይችላሉ። በተማሪ አካውንት ላይ ከበፊቱ የትምህርት አመት የተረፈ ማንኛውንም ገንዘብ ለክፍያ መጠቀም ይቻላል። ት/ቤት ከመጀመሩ አስቀድሞ በተማሪ አካውንት ላይ የቅድሚያ ክፍያ ማስገባት/መክፈል ይቻላል።

**ስለ ቼክ ተቀባይነት ፖሊሲ:** ለምግብ የሚከፈል ቼክ፦ ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የተማሪ መታወቂያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል ባንክ ሳይቀበል ቀርቶ ተመላሽ የሚደረጉ የክፍያ ቼኮች ለተከሰተው ወጭ ማካካሻ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ። የሜሪላንድ ስቴት በኤሌክትሮኒክስ ዴቢት ካርድ ወይም የወረቀት ድራፍት የሚከፈል የ $25 ክፍያ ለአካውንቱ እንዲከፈል ይፈቅዳል። እርስዎ ለካፍቴሪያ ሂሳብ በቼክ ሲከፍሉ እነኝህን መመሪያዎች መቀበልዎን ያረጋግጣል። ስለ እኛ የቼክ አቀባበል ፖሊሲ ማናቸውም ጥያቄ ካለዎት እባክዎ CHECKredi at 1-800-239-1222 ይደውሉ።

**ቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም፦**

- MySchoolBucks.com፣ በክሬዲት ካርድ ቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም የኦውታረመረብ አገልግሎት ይጠቀሙ። ወላጆችም የምግብ አካውንት ሂሳባቸውን ለመፈተሽ፣ ክፍያዎችን በተደጋጋሚ ለመክፈል፣ እና ለሌላም ተጨማሪ ነገሮች መመዝገብ ይችላሉ። ለመመዝገብ ይህንን በይነመረብ ይክፈቱ። MySchoolBucks.com
- ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ ይሙሉ እና ለካፊቴሪያ የሚከፈል ቼክ ወይም የገንዘብ ክፍያ ማዘዣ ይጨምሩበት። ስለቼክ ክፍያ ፖሊሲ ከዚህ በታች ያለውን መመሪያ ይመልከቱ።

**ከአሁን በኋላ MCPS ላልተመዘገበ ተማሪ ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ወይም ቀሪ ሂሳብ ክፍያ ለመጠየቅ፣ DFNHelpDesk@mcpsmd.org ኢሜይል ያድርጉ**

**የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን አገናኝ/ሊንክ ይመልከቱ፦**

- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/food-and-nutrition (CEP የትምህርት ቤቶች ዝርዝር፣ የምግብ ዝርዝር፣ የአመጋገብ መረጃ እና ሌሎችንም ይመልከቱ)
- www.MySchoolBucks.com (የምግብ ሂሳብ ቅድመ ክፍያ ለመፈጸም፣ በአካውንት ያለውን የሂሳብ ሚዛን ለማወቅ እና የክፍያ ሁኔታዎችን ለማረጋገጥ)
- በተጨማሪ ስለ አልሚ ምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)፣ ጊዜያዊ የገንዘብ ድጋፍ (TCA)፣ የሴቶች፣ የጨቅላ ህፃናት እና የልጆች ፕሮግራም (WIC) እና/ወይም የህክምና ፕሮግራሞችን መረጃ ለማግኘት እባክዎ **1-800-332-6347 ይደውሉ፤ ወይም ይህን በይነመረብ** https://dhs.maryland.gov/ ይቃኙ።

*ይህ ተቋም በእኩልነት የሚያገለግል ድርጅት ነው።*

**በትምህርት ቤት ካፌቴሪያ "A LA CARTE ምግቦች" የቅድመ ክፍያ ቅጽ**

እባክዎ ቼኩ ላይ ለልጅዎ ት/ቤት ካፍቴሪያ የሚከፈል ብለው ይጻፉበት (ለምሳሌ፡- Gaithersburg High School Cafeteria) "a la carte ምግቦች" ለመክፈል የሚያገለግሉ ቼኮች አድራሻ እና ስልክ ቁጥር መያዝ አለባቸው። እባክዎን የልጅዎን የመጀመሪያ ስም፣ የአያት ስም እና የተማሪ መታወቂያ ቁጥር በቼኩ ፊት ለፊት ላይ ይጻፉ። ይህ ቼክ ለካፍቴሪያ ክፍያ/ግዢ ብቻ ነው። እባክዎን እያንዳንዱን ተማሪ በተለይ በመመዝገብ ክፍያውን ለካፍቴሪያ ማናጀር ያቅርቡ። እናመሰግናለን!

የተማሪ ስም ______________________ የመታወቂያ ቁጥር ______________ መጠን $ ______________

የተማሪ ስም ______________________ የመታወቂያ ቁጥር ______________ መጠን $ ______________

የተማሪ ስም ______________________ የመታወቂያ ቁጥር ______________ መጠን $ ______________

የወላጅ/የሞግዚት ስም ______________________________ የስልክ ቁጥር ______________